የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፮
አዲስ አበባ–መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 46
ADDIS ABABA–8th April, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፮/፲፱፻፺፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በሄሌኒክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በቱሪዝም መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ........ ገጽ ፪ሺ፩፻፵፫

## CONTENTS

Proclamation No. 326/2003

Ratification of the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Hellenic Republic on Cooperation in the Field of Tourism Proclamation ........ Page 2143

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፮/፲፱፻፺፭

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በሄሌኒክ ሪፐብሊክ መካከል በቱሪዝም መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በሄሌኒክ ሪፐብሊክና በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል ወዳጅነትና ትብብርን ለማስፋፋት የሚያስችሉ መሠረታዊ ስምምነቶችን ከሄሊኒክ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር የተፈራረመ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ መንግሥት በተለያዩ መስኮች የጋራ ጥቅምን መሠረት ያደረገ ትብብርን ለማስፋፋት ያለውን ፈቃደኝነት በተደ ጋጋሚ የገለጸ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በሄሌኒክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በቱሪዝም መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወሰነ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በሄሌኒክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በቱሪዝም መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፮/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 326/2003
### A PROCLAMATION FOR THE RATIFICATION OF THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE HELLENIC REPUBLIC ON COOPERATION IN THE FIELD OF TOURISM

WHEREAS, the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has entered into basic Agreement with the Government of the Hellenic Republic for the promotion of friendly relations and cooperations among the people of the two countries;

WHEREAS, the Government of Ethiopia has expressed its willingness to develop cooperations in various fields in conformity with mutual benefits;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has accepted the ratification of the agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Hellenic Republic on Cooperation in the field of Tourism at its session held on 8th day of April, 2003;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Ratification of the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Hellenic Republic on Cooperation in the Field of Tourism Proclamation No. 326/2003."

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ስምምነቱ ስለማጽደቅ</u>

ህዳር ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም በሄሌኒክ ሪፐብሊክ መንግሥትና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በቱሪዝም መስክ ትብብር ለማድረግ የተፈረመውን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በዚህ አዋጅ አጽድቋል።

፫· <u>የቱሪዝም ኮሚሽነር ሥልጣን</u>

የቱሪዝም ኮሚሽነር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Hellenic Republic on Cooperation in the Field of Tourism signed on 20th November 1998, is hereby ratified by the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

3. *Power of the Tourism Commissioner*

The Tourism Commissioner is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 8th day of April, 2003.

Done at Addis Ababa, this 8th day of April, 2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE